# የNE 130th St እና NE 125th St ተንቀሳቃሽነት እና ደህንነት ፕሮጀክት

2024




## ወደ ሰፈራችሁ እየመጡ ያሉ የእግር ጉዞ፣ ብስክሌት የመጋለብ እና የሕዝብ መጓጓዣ ማሻሻያዎች!

በNE 130th St፣ Roosevelt Way NE እና NE 125th St ከ1st Ave NE እስከ Lake City Way NE በኩል ማሻሻያዎችን እያደረግን ነው! እነዚህ ለውጦች በእግር ለሚሄዱ፣ ቢስክሌት ለሚጋልቡ፣ የሚያንከባልሉ እና አውቶቡስ ለሚወስዱ ሰዎች የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀላል ያደርገዋል። እንዲሁም ከI-5 አቅራቢያ ከሚገኘው NE 130th St ወደ አዲሱ የቀላል ባቡር ጣቢያ እንዲደርሱ ደግሞ ይረዳዎታል። በየቀኑ ወደ 4,000 የሚጠጉ ተሳፋሪዎች ይጠበቃሉ፣ 90% ተሳፋሪዎች በእግራቸው የሚሄዱ፣ ብስክሌት የሚጋልቡ ወይም በሕዝብ መጓጓዣ የሚወስዱ ናቸው።

የሚከተሉት ማሻሻያዎች የፕሮጀክቱ አካል ናቸው:-

- የተጠበቁ የብስክሌት መስመሮች ከኮንክሪት ማገጃዎች ጋር የቢስክሌት ግልቢያን የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ
- ለአውቶቡሶች ቅድሚያ ጅምር እንዲሆኑ የአውቶቡስ አገልግሎት ማሻሻያ አዳዲስ እና የተሻሻሉ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች፣ የአውቶቡስ ብቻ መስመሮች፣ እና የምልክት ማሻሻያዎች
- ከባድ እና ገዳይ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያግዝ ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ እና መሰቀለኛ ማቋረጫ ንድፎች
- በእግር ለሚሄዱ፣ ብስክሌት ለሚጋልቡ፣ እና ለሚያንከባልሉ ሰዎች፣ እና የተሻሻሉ ምልክቶች ከመኪናዎች እና ከጭነት መኪናዎች ፊት ለፊት እንዲሄዱ የሚያስችል አዲስ ምልክቶች ጋር ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ ማቋረጫዎች
- የእግረኛ መንገድ ጥገናዎች እና አንዳንድ ቦታ ላይ አዲስ የኩርባ መወጣጫዎች

**ድህረ ጣቢያችንን ለመጎብኘት የQR ኮድን ይቃኙ። ስለ ፕሮጀክቱ ለማወቅ እና ለፕሮጀክት ዝመናዎች መመዝገብ ይችላሉ።**

**በእነዚህ በሚከተሉት መንገዶች መሳተፍ ይችላሉ:-**

- **አንድ የጎረቤት ብቅ-ባይ ክስተትን ይቀላቀሉ**
- **አንድ የማህበረሰብ ስብሰባ ይቀላቀሉ**
- **በአንድ የቡድናችን የስፈር ጉብኝት ወቅት ያግኙን**

**የፕሮጀክት መገናኛ:-**
ድሩ ኘንሁይስ (Drue Nyenhuis)
NE130thSt_NE125thSt_Project@seattle.gov
(206) 400-7515 www.seattle.gov/transportation/NE130thMobilityProject

Seattle Department of Transportation

King County METRO

# የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳ:-

| እቅድ ማውጣት | | ንድፍ | | ግንባታ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዋናው (Master) እቅድ(ዶች) | የፕሮጀክት ልማት አካሄድ | ቀደምት ንድፍ | የመጨረሻ ንድፍ | ቅድመ-ግንባታ | በ - ወቅት | ማጠቃለል |

እዚህ ነን

- **እቅድ ማውጣት (2023):** ከማህበረሰቡ በተገኘ ግብአት የደህንነት እና የተደራሽነት ማሻሻያዎችን ነድፈናል።
- **ንድፍ (2023-2025):** ለማህበረሰብ ግብረ መልስ ለውሳኔ የንድፍ ሀሳቦችን መፍጠር እና መጋራት።
- **ግንባታ (2025-2026*):** የግንባታ መርሃ ግብሮችን፣ እንቅስቃሴዎችን እና ተፅዕኖዎችን እናካፍላለን።
- **የቀላል ባቡር አገልግሎት ይጀምራል (2026):-** በNE 130th St Infill ጣቢያ ላይ ለወቅታዊ መረጃ የሳውንድ ትራንዚት (Sound Transit) ድህረ ገጽን ይጎብኙ።

* የግንባታ መርሃ ግብሮች በሠራተኞች እና በቁሳቁስ አቅርቦት ላይ በመመስረት ሊለወጡ ይችላሉ።

ይህ ፕሮጀክት በNE 130th St እና Interstate 5 መካከል በሚገኘው በኖርዝአከር ፓርክ ላይ አነስተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል። በ 1st Ave NE እና NE 130th St ጥግ ላይ እና በInterstate 5 መወጣጫ አጠገብ ያሉ ጥቃቅን ክለሳዎች በሲያትል መናፈሻዎች እና መዝናኛ ንብረቶች ውስጥ ቋሚ ለውጦችን ይፈልጋሉ:-

- በ1st Ave NE እና NE 130th St ጥግ ላይ በግምት 72 ካሬ ጫማ የ Northacres Park ንብረትን የሚጠቀም አዲስ የአሜሪካ የአካል ጉዳተኛነት ሕግ (ADA)-የሚያሟላ የኩርባ መወጣጫ መትከል።
- ሰፋ ያለ የመራመጃ ቦታ ለመስጠት እና ለተዘመነው የምስራቅ አቅጣጫ ተሽከርካሪ መስመሮች በቂ ቦታ ለመስጠት በInterstate 5 አጠገብ በNE 130th St ላይ የእግረኛ መንገድ መወጣጫ እንደገና መገንባት።

በ1966 የዩ ኤስ የመጓጓዣ መምሪያ (USDOT) ህግ በአንቀጽ 4(f) ስር de minimis (ከግንዛቤ የማይገባ) በኖርዝአከር ፓርክ ውስጥ ያሉ ጥቃቅን ለውጦች ተወስነዋል።
ከግንዛቤ የማይገባ de minimis ተፅዕኖ በአንቀጽ 4(f) ስር እንድ ንብረቱን ለመጠበቅ ብቁ የሆኑትን ባህሪያት፣ የጥራት መለያ፣ ወይም ተግባራት ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽእና የማያሳድር ነው። የፌዴራል የድጋፍ ገንዘብ ለሚያገኙ ፕሮጀክቶች አንቀጽ 4(f) ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

**የፕሮጀክት መገናኛ:-**
ድሩ ኘንሁይስ (Drue Nyenhuis)
NE130thSt_NE125thSt_Project@seattle.gov
(206) 400-7515 www.seattle.gov/transportation/NE130thMobilityProject

Seattle Department of Transportation

King County METRO